# ሽሮ ነው ፤ ሽሮ ነው

ምነው አልሰማኝም ፤ ለታቦት ተስዬ
አታምጪው እባክሽ ፤ ይቅርብን እምዬ
እሱን ለመሸከም ፤ ሰልችቷል ገላዬ ።

ስዬ ላሳይሽ ወይ ፤ የምስሉን ክፋት
እንኳን ለኔና አንቺ ፤ አይበጅ ለጠላት
ወስዶ ይዘፍቀናል ፤ ከነበረበት ።

ገብሩ ይሉናል ፤ ምን እንገብራቸው
እስከዛሬ የበሉት ፤ አልጠቅም ብሏቸው ።

የሚከፍለው ያጣ ፤ ቤሳ የሌለው
ምን በድሎ ይሆን ፤ መከራ አገኘው
አስራት ክፈል አሉት ፤ በየነ ዳኛው ።

ብርቱካን ለሽታ ፤ ነበር ለናሙና
ጣዕሙ ተለውጦ ፤ ቃናው ለወጠና
ተጥሎ ተገኘ ፤ መራራ ሆነና ።

መላዕክት ያወጡታል ፤ ስሙን ለሰው ልጅ
መራራ ያሉትም ፤ ቀድመው ቢያውቁት እንጂ ።

ከኛ ዘንድ አትምጡ ፤ መድሃኒት ፍለጋ
የተጠየቀውን ፤ ላትከፍሉ ዋጋ
አትመላለሱ ፤ በነጋ በነጋ ።

ላንግባባ ነገር ፤ እረፈደ ቀኑ
ለመዳብ አይሆንም ፤ የወርቅ ሚዛኑ
መሸ እንግዲ ፤ እንሂድ ፤ ጨልሟል ብርሃኑ ።

ተኩላ ታይቷል አሉ ፤ ትላንት መንደራቸው
ከብቶቹን ሰብስበህ ፤ በረት አስገባቸው
ወይፈኑን ጊደሯን ፤ ሁሉን አንድአርጋቸው
መለስ ብሎ ሄዶ ፤ እንዳይበትናቸው ።

ስንፍና ካልሆነ ፤ ወይ አለማስተዋል
ታሪካችን ብዙ ፤ ማን ጽፎ ይዘልቀዋል
ሰው ማስታወሻ እንጂ ፤ መርሻ መች ያሻዋል ።

አቻምናም ዘንድሮም ፤ መቼም አልተማረ
የራሱ ቢያልቅበት ፤ እየተበደረ
ሽመተ ፤ ነገደ ፤ መልሶ ከሰረ
ምነው ለጎበዜ ፤ ሚስጥር ተሰወረ ።

ለኔ አላማረኛም ፤ የሰው ሁሉ አመሉ
የጎበዝ አለቃ ፤ ፊታውራሪ ሁሉ
ለዘመቻ ታጥቀው ፤ ጃሎ እንዳላሉ
ምን ተገኘ ዛሬ ፤ መለስ ፤ መለስ አሉ?

የማርያምን ጽዋ ፤ ልንበላ ልንጠጣ
መልክት ቢላክበት ፤ ድርሻውን ሊያዋጣ
ከጎተራው ሞልቶ ፤ እህሉን ሳያጣ
ድግሱን ሊያበላሽ ፤ ዘሩን ይዞ መጣ።

ስንዴውና ገብሱ ፤ ኑግና ሱፉን
ተቆልቶ ስንበላው ፤ ጣዕም ያለውን
ነጣጥለው አመጡት ፤ ለይተው ዘሩን
ወዙም ፤ መልኩም ጠፋ ፤ አጣ ውበቱን ።

ድልሁ ለብቻው ፤ ይፋጃል ከፉ ነው
ዘይቱም እንደዚያው ፤ ለጤና ጠንቅ ነው
ተደባለቆ ነበር ፤ ወጡ ወጥ የሆነው
ሁሉን የሚስማማ ፤ ሽሮ ነው ፤ ሽሮ ነው ።

ከብላቴን ጌታ መርቆርዮስ